# ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሽ ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 969/2015

Implementation of Resettlement for Returning Citizens Affected by Displacement Directive No. 969/2015

የፍትሕ ሚኒስቴር
Ministry of Justice

ግንቦት 23፥ 2015

## መመሪያ ቁጥር 969/2015

## ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሽ ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 969-2015

በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012 መሰረት ተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች ተገቢ የጤና፣ የማህበራዊ አገልግሎት፣ የህግና ሥነ-ልቦና ምክርና ድጋፍ፣ ጊዜያዊ መጠለያ፣ የኢኮኖሚ ድጋፍ እና መሰል አገልግሎቶችን እንደሚያገኙ የተደነገገ በመሆኑ፤

በርካታ ኢትዮጵያውያን ወደ ተለያዩ ሀገራት ፈልሰው የተለያዩ ጉዳቶችና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተፈጽሞባቸውና ተጋልጠው እየተመለሱ በመሆኑና ከጉዳታቸው አገግመው ወደማህበረሰቡ በዘላቂነት ተመልሰው እንዲቀላቀሉ የማህበራዊ፤ የስነ ልቦና እና የኢኮኖሚ ድጋፎች እንዲያገኙ ማስቻል አስፈላጊ በመሆኑ፤

በተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች መልሶ ማቋቋም ሂደት ተሳታፊ የሆኑ ባለድርሻ አካላት የሚኖራቸውን ሚና መግለጽ፤ በመካከላቸው ስለሚኖረው ቅንጅታዊ አሰራር መወሰን እና ወጥነት ያለው የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች መልሶ ማቋቋም ድጋፍ ማዕቀፍ የሚሸፈኑ ጉዳዮችን እና የድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓቱን በዝርዝር በመወሰን መልሶ ማቋቋሙን ፍትሀዊ፣ ተደራሽ እና ወጥነት ባለው መልኩ ማከናወን በማስፈለጉ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፍትሕ ሚኒስቴር በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 46(2) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሽ ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም የወጣ መመሪያ ቁጥር 969/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1) **"አዋጅ"** ማለት በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012 ነው፤
2) **"ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሽ"** ማለት በአዋጁ ከተመለከቱት የወንጀል ድርጊቶች አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የተፈጸመበት እና አካላዊ፣ ስነልቦናዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የደረሰበት ወይም የመብት ጥሰት የተፈጸመበት ወይም ወንጀል ባይፈጸምበትም ለወንጀሉ የተጋለጠ ወይም ሊጋለጥ የሚችል በመሆኑ በአዋጁ የተመለከተው ጥበቃና ድጋፍ የሚያስፈልገው ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰ ወይም እንዲመለስ የተደረገ ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነው፤
3) **"ብሔራዊ የትብብር ጥምረት"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 35 (1) መሰረት የተቋቋመው በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና በህገ ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ መላክ ወንጀል መከላከልና መቆጣጠር ብሔራዊ የትብብር ጥምረት ነው፤
4) **"የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የስራ ቡድን"** ማለት በፍልሰት ብሔራዊ የትብብር ጥምረት አባላትንና የሥራ ቡድኖችን አደረጃጀት እና አሰራር ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 563/2013 አንቀጽ 5 (1)3) መሰረት የተደራጀው ነው፤
5) "**ተጎጂን መልሶ ማቋቋም**" ማለት ተጎጂን ከጉዳት በፊት ወደነበረበት የማህበረሰብ ክፍል ወይም ወደመደበኛ መኖሪያው የመመለስና የስነ-ልቦና፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ እንዲያገኝ የማድረግ ተግባር ነው፤
6) "**ተጋላጭነት**" ማለት አንድን ተጎጅ ከፍልሰት ተመላሽ በእድሜው፣ በጾታው፣ በአካላዊ ሁኔታው፣ በጤናው፣ በስሩ በሚተዳደሩ ሰዎች መኖር፣ በኢኮኖሚ ደረጃው፣ ወይም በተፈጸመበት ወንጀል ወይም ጥቃት ምክንያት ወደነበረበት ማህበረሰብ ተመልሶ ሲቀላቀል ድጋፍ ካልተደረገለት በቀር ችግርን የመቋቋም አቅሙ ደካማ የሆነ ወይም ካለበት ሁኔታ የማገገም አቅሙ አነስተኛ የሆነ ተመላሽ ሁኔታን ይመለከታል፤
7) **"ሕጻን"** ማለት ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው፤
8) በአዋጁ አንቀጽ 2 እና በፍልሰት ጉዳዮች ላይ በወጡ ሌሎች ህጎች የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደየአግባብነታቸው ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
9) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አገላለፅ ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ፡-

1) በተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች፤ እና
2) በፌዴራል፣ በክልልና በከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ በአዋጁና አግባብነት ባለው ሌላ ህግ መሰረት ተጎጂ የፍልሰት ተመላሾችን መልሶ የማቋቋም ተግባር እና ኃላፊነት በተሰጣቸው አካላት፤

ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

4. <u>መርሆዎች</u>

ተጎጂ የፍልሰት ተመላሾችን መልሶ የማቋቋም ድጋፍ አገልግሎት አሰጣጡ የሚከተሉትን መርሆዎች መከተል ይኖርበታል፡-

1) ፈቃደኝነት፤
2) ፍላጎትን ታሳቢ ያደረገ፤
3) እኩልነት፤
4) አሳታፊነት፤
5) ጥገኝነትን የማያበረታታ፤
6) አካታችነት ወይም ልዩ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ፤
7) የተጎጂን ሚስጥር የጠበቀ፤
8) ሰብዓዊነት፤
9) ፍትሃዊነት፤ እና
10) ተጠያቂነት።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለመልሶ ማቋቋም ድጋፍ አሰጣጥ</u>

### <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

### <u>ተጎጂ የፍልሰት ተመላሾችን ስለመመዝገብ</u>

5. <u>ተጎጂ የፍልሰት ተመላሾችን ስለመመዝገብ</u>

1) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተመላሾች ፈቃድ ወይም በመዳረሻ ሀገራት ህግ አስገዳጅ ሁኔታ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ የሚደረጉ ዜጎችን መረጃ በመሰብሰብ አደራጅቶ ለኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት እና ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያስረክባል።

2) የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ወይም በራስ ፍቃድ ወይም በአስገዳጅ ሁኔታ ወደ ሀገራቸው በአየርና በየብስ (በድንበር ኬላዎች) በኩል የሚመለሱ ዜጎች ለመልሶ ማቋቋም የድጋፍ አሰጣጥ አመቺ እንዲሆን ታስቦ በተዘጋጀ የመመዝገቢያ ቅጽ መሠረት ምዝገባ ያከናውናል፤ የተመዘገበውን የተመላሾች መረጃ ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያስረክባል።

3) የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የተረከበውን መረጃ ወደ መረጃ ቋት በማስገባት በየደረጃው ድጋፍ ለሚሰጡ የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የፌዴራልና የክልል ተቋማት እንዲደርስ ያደርጋል።

4) ከዚህ በላይ በተጠቀሱት መንገዶች ተለይተው ሳይመዘገቡ ወደ ሀገራቸው የገቡ ተመላሾችን በተመለከተ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሠረት ተመላሽ መሆናቸው ተረጋግጦ በየአካባቢው ባሉ በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ይመዘገባሉ፤ መረጃውም በየደረጃው ለወረዳ/ከተማ፣ ዞን፣ ክልልና ፌደራል እንዲደርሰ ይደረጋል።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ወደ ሀገራቸው ገብተው በጽኑ ህመም ምክንያት ስለ ራሳቸው መረጃ መስጠት የማይችሉ ተመላሾች አስፈላጊውን የህክምና አገልግሎት ካገኙ በኋላ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል መረጃቸው ወደ መረጃ ቋት እንዲገባ ይደረጋል።

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት የሚመለሱ ተመላሾችን ለመቀበል፣ ለመመዝገብ እና ፍላጎት ልየታ ስራ ያመች ዘንድ አየር መንገድና ድንበር ኬላዎች ላይ አገልግሎት መስጫ ዴስክ ይቋቋማል።

6. <u>በምዝገባ ወቅት ስለሚሰጡ አስቸኳይ ድጋፎች</u>

1) በአንቀጽ 5 መሰረት የመመዝገብ ተግባርና ሃላፊነት የተሰጣቸው አካላት አስቸኳይ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተመላሾች ድጋፉ እንዲሰጣቸው ያደርጋሉ፤ ያመቻቻሉ።

2) ለዚህ ድንጋጌ አላማ "አስቸኳይ ድጋፍ" ማለት አንድ ተጎጂ የፍልሰት ተመላሽ በየብስም ሆነ በአየር ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ ወዲያውኑ የሚያስፈልገው የህክምና፣ የምግብ፣ የንጽህና መጠበቂያ፣ የአልባሳት፣ የጊዜያዊ መጠለያ እና መሰል ድጋፍ ማለት ነው።

7. <u>ስለመመዝገቢያ ቅጽና ስለሚመዘገቡ መረጃዎች</u>

1) የተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች ምዝገባ የተመላሾችን ማንነት፣ የተመለሱበት ሁኔታ፣ ጊዜ (ቀን፣ ወርና ዓመተ-ምህረት)፣ በሀገር ውስጥ የመኖሪያ አድራሻ (ስልክ፣ ኢሜልና ሌሎች መገናኛ መንገዶች) እና በቀላሉ ሊለዩ የሚችሉ የተጋላጭነት ሁኔታዎች እና ተያያዥ መረጃዎችን እንዲይዝ ተደርጎ የመመዝገቢያ ቅፅ ይዘጋጃል።

2) ተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች ተመላሽ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጡ አስፈላጊ የጉዞ ሰነድ ቅጂዎችን አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

3) ተጎጂ የፍልሰት ተመላሾችን የመመዝገብ ሀላፊነት ያለበት ማንኛውም ተቋም በቅጹ መሠረት የተሟላ መረጃ መዝግቦ ለሚመለከተው ተቋም የማስተላለፍ ግዴታ አለበት።

8. <u>ተመላሽነትን ስለማረጋገጥ</u>

በዚህ መመሪያ መሠረት አንድ ተመላሽ ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሽ ዜጋ ሆኖ የሚለየው ተመላሹ ከሚከተሉት ውስጥ ቢያንስ አንዱን አሟልቶ ሲገኝ ነው፡-

1) ከውጭ ሀገር ወደ ሀገሩ ስለመመለሱ ከኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ህጋዊ ማሥረጃ ማቅረብ የሚችል፤

2) ከውጭ ሀገር ወደ ሀገሩ ስለመመለሱ ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተዘጋጀ የተመላሽነት ማረጋገጫ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፤

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ '1 እና 2' ላይ የተጠቀሰውን ማስረጃ ማቅረብ የማይችል አመልካች የፍልሰት ተመላሽ ስለመሆኑ አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች (ከውጭ ወደ ሀገር ቤት በስሙ ገንዘብ የላከበት መረጃ፣ የጉዞ ታሪክ፣ ከነበረበት ሀገር እንዲወጣ የሚያዝ ሰነድ እና ሌሎች ተያያዥ ማስረጃዎች) ማቅረብ የሚችል።

9. <u>ህጻናትን ስለመመዝገብ</u>

በአንቀጽ 8 ላይ የተጠቀሰውን ማስረጃ ማቅረብ የሚችል ህፃን ይዞት በመጣው ግለሰብ ወይም ማንኛውም ያገባኛል በሚል አካል አቅራቢነት ምዝገባው ይከናወናል።

## 10. የአዕምሮ ህመምተኛ ስለመመዝገብ

በአንቀጽ 8 ላይ የተጠቀሰውን ማስረጃ ማቅረብ የሚችል የአዕምሮ ህመምተኛ የሆነ ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሽ ይዞት በመጣው ግለሰብ ወይም ማንኛውም ያገባኛል በሚል አካል አቅራቢነት ምዝገባው ይከናወናል።

## 11. የምዝገባ ጊዜ

ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች በማንኛውም ጊዜ በአንቀጽ 8 የተጠቀሡትን መረጃዎች ይዘው በመቅረብ በአንቀጽ 5 በተመላከቱት የመመዝገቢያ አማራጮች አማካኝነት ይመዘገባሉ።

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የተጎጅ ከፍልሰት ተመላሾች ተጋላጭነትን ስለመወሰን

## 12. ተጋላጭነት ስለሚወሰንበት ሁኔታ

1) ለአንድ ከፍልሰት ተመላሽ ዘላቂነት ያለው የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ ከመሰጠቱ በፊት ተመላሹ ያለበትን የተጋላጭነት ሁኔታ እና የተጋላጭነት ደረጃ የመለየት ስራ ይከናወናል።

2) ተጋላጭነትን የመለየት ስራ የሚከናወነው ከፍልሰት ተመላሹ እድሜ፣ ጾታ፣ አካላዊ ደህንነት፣ የጤንነት ሁኔታ፣ የእርግዝና ሁኔታ፣ የቤተሰብ ሁኔታ (ጥገኞች መኖር)፣ የገቢ ሁኔታ፣ የአዕምሮ ሁኔታ፣ ለተለያዩ አካላዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጥቃቶች ተጋልጦ የመቆየት ሁኔታ እና ሌሎች ጠቅላላ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ገብቶ ነው።

3) የተጋላጭነት ሁኔታ የሚወሰነው እንዳስፈላጊነቱ ከፍልሰት ተመላሹን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ፣ በምልከታ፣ አስፈላጊ ሰነዶችን በማጤን፣ አስፈላጊ የጤና ምርመራ በማከናወን፣ የባለሙያዎችን አስተያየት በመጠየቅ፣ የተመላሹን ቤተሰብ፣ የሚመለከታቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች እና ተቋማት ቃለ-መጠይቅ በማድረግ ነው።

4) የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአንቀጽ 5 መሰረት ከፍልሰት ተመላሹን በሚመዘግቡበት ወቅት በመጀመሪያ ደረጃ ልየታ የመዘገቧቸው የተጋላጭነት ሁኔታዎች በቂ ሁነው ከተገኙ ያንን መሰረት በማድረግ የተጋላጭነት ደረጃ ይለያል።

5) ከፍልሰት ተመላሹ ወደአካባቢው ከተመለሰ በኋላ ተጋላጭነት የመለየት እና የመወሰን ስራ በወረዳ/ከተማ ደረጃ በተጎጂዎች እንክብካቤና መልሶ-ማቋቋም የስራ ቡድን አባላት ይወሰናል፤ በዚህ አግባብ ሲወስኑም ሌሎች ባለሙያዎችን በተለይም የህክምና፣ የስነ-ልቦናና ማህበራዊ፣ የህግ እና ሌሎች አስፈላጊ ባለሙያዎችን ምክር መጠየቅ ይኖርባቸዋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የሚካተቱበት የልየታ ኮሚቴ ሊያደራጁ ይችላሉ።

## 13. <u>የተጋላጭነት ደረጃዎች</u>

የአንድ ተመላሽ የተጋላጭነት ደረጃ ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ተብሎ ሊወሰን የሚችል ሲሆን እንደሚከተለው የሚከናወን ይሆናል።

1) የሚከተሉት ተመላሾች ከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ተብለው ይመደባሉ፡-

ሀ/ ጠባቂ የሌላቸው እና ከቤተሰባቸው የተነጠሉ ህጻናት፤

ለ/ በፍልሰት ህይወት ቆይታቸው ለከፍተኛ ጥቃት ተጋልጠው ለከፍተኛ አካላዊ ጉዳት ወይም ለከባድ ህመም (አብሯቸው ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ህመም) የተጋለጡ፤

ሐ/ በሰዎች የመነገድ ወንጀል ተጎጅ የሆኑ እና በዚህም ምክንያት ከፍተኛ አካላዊ ወይም ስነ-ልቦናዊ ጉዳት ወይም ከፍተኛ የአዕምሮ ህመም ያለባቸው (ራሳቸውን መጠበቅ የማይችሉ) ሰዎች፤

መ/ ቋሚ ከባድ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተመላሾች፤

ሠ/ የሚደግፏቸው ቤተሰብ የሌላቸው እና ምንም አይነት የገቢ ምንጭ ወይም ካፒታል የሌላቸው አዛውንቶች፤ ወይም

ረ/ ከአምስት አመት በታች እድሜ የሆኑ ህጻናት ያሏቸው እናቶች ወይም ነፍሰ ጡር ሴቶች ሆነው የሚደግፋቸው ቤተሰብ የሌላቸው ወይም ምንም አይነት የገቢ ምንጭ የሌላቸው ወይም ካፒታል የሌላቸው፤

2) የሚከተሉት ተመላሾች መካከለኛ ደረጃ ተጋላጭ ተብለው ይመደባሉ፡-

ሀ/ ቤተሰብ ያላቸው ህጻናት ሆነው ቤተሰቦቻቸው ምንም አይነት የገቢ ምንጭ ወይም ካፒታል የሌላቸው፤

ለ/ በከፊል ሀላፊ የሆኑ አዕምሮ ህመምተኛ ተመላሾች፤

ሐ/ መለስተኛ ቋሚ የአካል ጉዳት ያለባቸው፤ ወይም

መ/ በፍልሰት ሂደት ለአካላዊና ስነ ልቦናዊ ችግር የተጋለጡ አዋቂ ተመላሾች (ከባድ ህመም ሆኖ ለረጅም ጊዜ አብሯቸው የማይቆይ) እና ምንም አይነት የገቢ ምንጭ ወይም ካፒታል የሌላቸው።

3) አዋቂ ተመላሾች ሆነው ምንም አይነት የገቢ ምንጭ ወይም ካፒታል የሌላቸው ተመላሾች ዝቅተኛ ደረጃ ተጋላጭ ተብለው ይመደባሉ::

14. <u>ለመልሶ ማቋቋም ድጋፍ ብቁ ስለመሆን</u>

1) አንድ ተመላሽ ለመልሶ ማቋቋም ድጋፍ ብቁ የሚሆነው የተጋላጭነት ደረጃው ከፍተኛ ወይም መካከለኛ ወይም ዝቅተኛ ሲሆን ነው።

2) በዚህ አንቀጽ ንዕስ አንቀጽ (1) መሰረት ለሶስቱም የተጋላጭነት ደረጃዎች የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ ለማድረግ የአቅም ውስንነት ካጋጠመ ድጋፉ በቅደም ተከተል ለከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ደረጃዎች ይሰጣል።

3) አንድ ተመላሽ ለመልሶ ማቋቋም ብቁ በሆነ ጊዜ የተጎጂ ከፍልሰት ተመላሽ እንክብካቤና መልሶ-ማቋቋም የስራ ቡድን ለተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ይመራል።

4) ተጋላጭ ያልሆነ ተመላሽ ለመልሶ-ማቋቋም ብቁ እንዳልሆነ ይቆጠራል።

15. <u>ፍላጎትን ስለመለየት</u>

1) የአንድ ተመላሽ የተጋላጭነት ደረጃ ከተለየ በኋላ ወይም እንደጉዳዩ ሁኔታ ወዲያውኑ የተጎጂ ከፍልሰት ተመላሽ እንክብካቤና መልሶ ማቋቋም የስራ ቡድን የተመላሹን የመልሶ ማቋቋም ፍላጎቶች ይለያሉ።

2) የፍላጎት ልየታ የሚከናወነዉ የእያንዳንዱን ተመላሽ ግላዊ ሁኔታ መሰረት ተደርጎ መሆን ይኖርበታል። ይህም የተመላሹን ፍላጎት፣ አቅም፣ ክህሎት፣ የትምህርት ደረጃ፣ የኢኮኖሚ ደረጃ፣ እና ሌሎች የሚያስፈልጉትን ነገሮች መሰረት ተደርጎ ይሆናል።

3) የፍላጎት ልየታ አሰራር የተመላሹን ፍላጎት ማዕከል ያደረገ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚገባ ሲሆን በተለይም መስራት የሚፈልግበትን የሥራ ቦታ እና የሥራ አይነት እንዲመርጥ ይደረጋል።

16. <u>ከፍላጎት ልየታ በኋላ ለድጋፍ ስለመላክ</u>

1) የተጎጂዎች እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም የስራ ቡድን የተመላሾችን ፍላጎት ከለየ በኋላ ተመላሹ የተለዩ ፍላጎቶቹን አገልግሎት ወደሚያገኝበት ተቋም ይልከዋል። ባለሙያው ይህንን ሲያደርግ አስፈላጊ መረጃዎችን (የተጋላጭነት እና የፍላጎት ልየታ ሪፖርት እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች) አያይዞ መላክ ይኖርበታል።

2) ተመላሹ ህጻን ወይም የአዕምሮ ህመምተኛ በሆነ ጊዜ ተመላሹን በሞግዚት ወይም ይመለከተኛል በሚል አካል አማካኝነት ለአገልግሎት የሚልክ ይሆናል።

3) ተመላሹ የአካል ጉዳተኛ በሆነ ጊዜ ባለሙያው አስፈላጊውን ድጋፍ አመቻችቶ ለአገልግሎት መላክ ይጠበቅበታል።

4) ተመላሹ በብሔራዊ የቅብብሎሽ ስርዓት መሰረት አገልግሎት እንዲያገኙ ይደርጋል።

5) ተመላሹ ለአገልግሎት ወደሌላ ተቋም ከተላከ በኋላ አገልግሎቱን በአግባቡ እያገኘ ስለመሆኑ የመከታተል ሀላፊነት የስራ እድል ፈጠራ ባለሙያው ይሆናል።

## <u>ንዑስ ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለመልሶ ማቋቋም ድጋፍ ማዕቀፎች</u>

17. <u>የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ ማዕቀፎች</u>

ተጎጂ የፍልሰት ተመላሽ መሆናቸው ለተረጋገጡ ዜጎች የሚሰጥ የመልሶ ማቋቋም የድጋፍ ማዕቀፍ የተጎጂዎችን ልዩ ፍላጎት፣ ነባራዊ ሁኔታ እና ያለውን ድጋፍ የመስጠት አቅም ያገናዘበ ሆኖ በሚከተሉት ዘርፎች ይከናወናል፡-

1) በየብስም ሆነ በአየር ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ የሚሰጥ ድጋፍ፤ እና
2) ወደ አካባቢያቸው /ቤተሰቦቻቸው በመመለስ የሚሰጥ ድጋፍ እና ወደየአካባቢያቸው /ቤተሰቦቻቸው ከተመለሱ በኋላ የሚሰጥ ድጋፍ።

18. <u>ለተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች ወደ ሃገራቸው ሲገቡ የሚደረግ ድጋፍ</u>

1) የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና በየደረጃው ያሉ የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር ለተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች ወደ ሃገራቸው ሲገቡ፡-

ሀ/ እንደየጉዳት መጠናቸው በመለየት ወደ መጡበት አካባቢ ወይም ወደ ቤተሰቦቻቸው እስከሚመለሱ ድረስ የሚያርፉበት ጊዜያዊ የመጠለያ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል።

ለ/ በዋናነትም ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በደረሰባቸው አካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና አእምሯዊ ጥቃት ምክንያት ችግር ውስጥ ያሉትን በመለየት ከችግሩ እንዲላቀቁ ለማስቻል የሥነ-ልቦና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን በመለየት የሥነ-ልቦና ምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል።

ሐ/ ለአልባሳት እና ለምግብ ፍጆታ የሚሆን አቅም የሌላቸውን ተመላሾች የመለየት ስራ በመስራት የአልባሳትና የምግብ አገልግሎት ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል።

መ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለተመላሾች የንጽህና መጠበቂያና ተመጣጣኝ የኪስ ገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል።

2) የጤና ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት ከፍልሰት ተመላሽ ዜጎች ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ አጠቃላይ የጤና ምርመራ በማድረግ ልዩ የህክምና ድጋፍ የሚያስፍልጋቸውን በመለየት በተለያዩ የህክምና መስጫ ተቋማት የጤና ምርመራ እና የህክምና ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል።

3) የፍትህ ሚኒስቴርና በየደረጃው የሚገኙ የፍትህ ተቋማት ለተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች ከህግ አንጻር ስላሏቸው መብቶች ግንዛቤ ይፈጥራሉ፤ ወንጀል መፈፀሙን የሚያመላክቱ መረጃዎች ካሉ ምርመራ እንዲጣራ ያደርጋሉ።

19. <u>ለተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች ወደየአካባቢያቸው /ቤተሰቦቻቸው በመመለስና ወደየአካባቢያቸው /ቤተሰቦቻቸው ከተመለሱ በኋላ የሚሰጥ ማህበራዊ ድጋፍ</u>

1) የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት፡-

ሀ/ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን የፍልሰት ተመላሾች በመለየት ወደ አካባቢያቸውና ቤተሰቦቻቸው እንዲቀላቀሉ ለማስቻል ወጪያቸው እንዲሸፈንላቸው ያደርጋል።

ለ/ ተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች ወደየአካባቢያቸው ሲመለሱ እና ከማህበረሰቡ ጋር የማቀላቀል ስራ ከተከናወነ በኋላ መጠለያ የሌላቸውና ቤት ተከራይተው ለሚኖሩ የምግብ ማብሰያ እና ሌሎች መሰረታዊ የቤት ውስጥ መገልገያ መሳሪያዎች እንዲሟላላቸው ያደርጋል።

ሐ/ የተመላሾችን አድራሻ በመለየት ለተመላሾች፣ ለቤተሰቦቻቸው እና ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር ወደየአካባቢያቸው በመመለስ ከቤተሰባቸውና ከማህበረሰቡ ጋር መልሶ የማገናኘት እና የማቀላቀል ስራ ይሰራል፤ በዚህ ሂደት ውስጥ ቤተሰብ ለሌላቸው እና የመኖሪያ ችግር ላጋጠማቸው ተመላሾች የአካባቢው አስተዳደር ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ጊዜያዊ የመኖሪያ ቤት ድጋፍ ያመቻቻል።

2) ፍትህ ሚኒስቴርና በየደረጃው የሚገኙ የፍትህ ተቋማት ከሚመለከታቸው የመንግስት እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር ነጻ የህግ አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን የፍልሰት ተመላሾች በመለየት የህግ አገልግሎት ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋሉ።
3) የትምህርት ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር ወደ ትምህርት መመለስ ለሚፈልጉና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተመላሾችን በመለየት ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ አስፈላጊ የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችና መሰል ድጋፎች እንዲሰጣቸው ያደርጋል።
4) የስራና ክህሎት ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ቴክኒክና ሞያ ትምህርት መውሰድ ለሚፈልጉና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተመላሾችን በመለየት ትምህርቱን እንዲከታተሉ አስፈላጊ የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችና መሰል ድጋፎች እንዲሰጣቸው ያደርጋል።

## 20. <u>ለተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች ወደየአካባቢያቸው /ቤተሰቦቻቸው ከተመለሱ በኋላ የሚሰጥ ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ</u>

1) የሥልጠና አገልግሎትን በተመለከተ የስራና ክህሎት ሚኒስቴርና በየደረጃዉ ያሉ ተቋማት:-

ሀ/ የተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች በቅጥር ወይም የራሳቸውን ስራ መፍጠር የሚያስችላቸውን የስራ ፈጠራ አስተሳሰብ ስልጠና በመስጠት ሊሰማሩ

የሚፈልጉበትን የስራ መስክ በመለየት የንግድ ሃሳብ እንዲያመነጩ፣ የንግድ እቅድ እንዲያዘጋጁና ወደ ስራ እንዲገቡ የሚያግዝ ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል።

ለ/ በስራ ዕድል ፈጠራ መመልመያ መስፈርት መሰረት በመመልመል የስራ እድል ፈጠራ አስተሳሰብ ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል።

ሐ/ የተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾችን የስልጠና ፍላጎት በየስራ መስኩ ዝርዝር በመለየት የፋይናንስና ብድር አጠቃቀም አጫጭር ስልጠና እንዲሰጣቸው ያደርጋል።

መ/ የተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾችን የስልጠና ፍላጎት በየስራ መስኩ ዝርዝር በመለየት አጫጭር የቴክኒካል ክህሎት ስልጠና እንዲሰጣቸው ያደርጋል።

2) የስራ እድል ፈጠራ ድጋፍን በተመለከተ የስራና ክህሎት ሚኒስቴርና በየደረጃዉ ያሉ ተቋማት፡-

ሀ/ ተመላሾች የራሳቸውን ስራ ለመፍጠር የንግድ ሃሳብ እንዲያመነጩና የንግድ እቅድ እንዲያዘጋጁ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ እንደየፍላጎታቸው የአደረጃጀት ድጋፍ በመስጠት የንግድ ፍቃድ እንዲያገኙ ያመቻቻል።

ለ/ የአደረጃጀት ድጋፉ በግላቸው መሰማራት የሚፈልጉትን የግል ኢንተርፕራይዝ እንዲያቋቁሙ እንዲሁም በጋራ ሆነው የመስራት ፍላጎት ያላቸውን የንግድ ማህበር እንዲያቋቁሙ ድጋፍ ያደርጋል።

ሐ/ በቅጥር የስራ እድል እንዲፈጠርላቸዉ ለሚፈልጉ ከፍልሰት ተመላሾችን ሊቀጥሩ የሚችሉ ድርጅቶችን በመለየትና የስራ ፍላጎትን በማጣጣም በቅጥር የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው ከቀጣሪ ተቋማት ጋር በማገናኘት የስራ ትስስር ይፈጥራል።

3) የፋይናንስ አቅርቦት ድጋፍን በተመለከተ የስራና ክህሎት ሚኒስቴር በየደረጃዉ ያሉ ተቋማት፡-

ሀ/ የተጎጂ ከፍልሰት ተመላሽ ዜጎች ያላቸውን ጥሪት በብድር አቅራቢ ተቋማት መቆጠብ የሚችሉበት ስርዓት በማመቻቸት በቆጠቡት የብር መጠን እና ባዘጋጁት የንግድ እቅድ መሰረት ለስራ ማስጀመሪያ የሚያስፈልጋቸውን ብድር በፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት እንዲመቻችላቸው ያደርጋል።

ለ/ ምንም ጥሪት የሌላቸዉ ተጎጅ ከፍልሰት ተመላሽ ዜጎች በጥሪት ማፍሪያ የስራ ዘርፎች በማሰማራት የቅድመ ብድር ቁጠባ እንዲያሟሉና ብድር እንዲያገኙ ይደረጋል ወይም ከተጎጅዎች ፈንድ የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል።

ሐ/ ከተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ጋር በመቀናጀት በተለያዩ ድርጅቶች የሚመለሱ ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች ለመልሶ ማቋቋሚያ የሚሰጣቸው ገንዘብ በሚያቀርቡት የንግድ እቅድ መሰረት ወደ ስራ ሊያስገባቸው የሚችል እና የመደበኛ የፋይናንስ ስርዓቱን በማያዛባበት አግባብ የተጎጂ ተመላሾች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ ስርዓት በመዘርጋት እንዲሰጣቸዉ ይደረጋል።

መ/ በተለያዩ የስራ ዘርፎች የተሰማሩና ለሚሰማሩ ከፍልሰት ተመላሽ ዜጎች በሚያቀርቡት የማምረቻ መሳሪያ ፍላጎት መሰረት ከማሽነሪ ሊዝ አቅራቢ ተቋማት እንዲመቻችላቸው ይደረጋል።

4) ሌሎች ድጋፎችን በተመለከተ የስራና ክህሎት ሚኒስቴርና በየደረጃዉ ያሉ ተቋማት፡-

ሀ/ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን ለተጎጂ የፍልሰት ተመላሽ ዜጎች የመስሪያና መሸጫ ቦታ አቅርቦት እንደየ አካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታና እንደ ተሰማሩበት የስራ መስክ ድጋፍ ይሰጣል፤ የአቅርቦት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች በኪራይ ወይንም በሌሎች አማራጮች ወደ ስራ እንዲገቡ ያደርጋል።

ለ/ ተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች ገበያ ተኮር ምርት እንዲያመርቱ፣ በአካባቢው ላይ የሚታየውን የገበያ እጥረት መፍታት እንዲችሉ እና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ድጋፍ ያደርጋል።

ሐ/ የሚያመርቷቸውን ምርቶች ለህብረተሰቡ ለማስተዋወቅ የሚችሉበትን ዘዴ በማመቻቸት በኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ በማሳተፍ ዘመናዊ የግብይት ስርዓትን እንዲከተሉ በየወቅቱ የመረጃና የምክር አገልግሎት እንዲሰጣቸው ያደርጋል።

መ/ ስልጠና ያገኙ ተጎጂ ተመላሾች በፍላጎታቸው መብታቸው ተከብሮ የውጭ ሀገር የስራ ስምሪት ድጋፍ ያመቻቻል።

## 21. <u>ከቤተሰባቸው ውጪ ከፍልሰት ተመላሽ ለሆኑ ህፃናት የሚደረግ ድጋፍ</u>

1) ከፍልሰት ተመላሽ ህፃናት ከተመለሱበት ጊዜ ጀምሮ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

2) የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ቤተሰባቸውን አፈላልጎ የመቀላቀል ስራ ይሰራል፤ ቤተሰቦቻቸው ሊገኙ ያልቻሉ ህጻናትን በተመለከተ ህጻናቱ በዘላቂነት የሚያድጉበትን ህጋዊ መፍትሔዎች በማፈላለግ ይተገብራል እና ሌሎች የህጻናቱን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ሁሉንዓቀፍ ድጋፎች ያደርጋል።

3) የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የስራና ክህሎት ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ዕድሜያቸው ከ15-18 ዓመት ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሽ ሆነው ትምህርታቸውን መቀጠል ለማይፈልጉ ህጻናት አግባብነት ያለውን የኢኮኖሚ ድጋፍ ያመቻቻሉ።

## <u>ንዑስ ክፍል አራት</u>

## <u>የተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች ድጋፍ አሰጣጥ እርከኖች</u>

### 22. <u>የተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች ድጋፍ አሰጣጥ እርከኖች</u>

ለተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች የሚሰጥ የድጋፍ ማዕቀፍ ከላይ በንዑስ ክፍል ሦስት ሥር በተለዩ የድጋፍ ዘርፎች ሆኖ ተጎጂ የፍልሰት ተመላሹን ፍላጎት መሠረት አድርጎ በሚከተሉት አራት የድጋፍ አሰጣጥ እርከኖች መሰረት ይፈፀማል።

### 23. <u>እርከን አንድ</u>

1) በዚህ እርከን ሥር የሚሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በሚመለከተው አካል ከተመዘገቡበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አንድ ወር የሚደረጉ የድጋፍ አገልግሎቶች ሲሆኑ የሚከተሉትን ያጠቃልላል:-

ሀ/ ስለሚያገኙት ድጋፍ እና የድጋፍ አሰጣጥ ግንዛቤ ማስጨበጥ፤

ለ/ የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ አገልግሎት ድጋፍ፤

ሐ/ የምግብ ማብሰያ መሣሪያዎች፤

መ/ ጊዜያዊ መጠለያ፣ አልባሳት እና ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ፤

ሠ/ የጤና ምርመራና የህክምና አገልግሎት፤

ረ/ የስነ-ልቦና ምክር አገልግሎት፤

ሰ/ የትራንስፖርት አገልግሎት ድጋፍ፤

ሸ/ ከቤተሰብና ከማህበረሰብ ጋር መልሶ ማገናኘት እና ማቀላቀል፤

ቀ/ የህግ ድጋፍ አገልገሎት::

24. <u>እርከን ሁለት</u>

1) በዚህ እርከን ሥር የሚሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች በመደበኛነት ወደሚኖሩበት አካባቢ ከደረሱ በኋላ ባሉት ሶሰት ወራት ጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ/ የትምህርት እና መርጃ መሣሪያዎች ድጋፍ፤

ለ/ የህይወት ክህሎት እና አስተሳሰብ ለውጥ ሥልጠና፤

ሐ/ በመሠረታዊ የሥራ ፈጠራ ክህሎት እና ንግድ ዕቅድ አዘገጃጀት፣ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ ክህሎት ሥልጠና፤

መ/ ተጎጂ የፍልሰት ተመላሾች ፍላጎትን መሠረት ያደረገ አጫጭር የቴክኒክ እና የሙያ ስልጠና አገልግሎት፤

ሠ/ ተጎጂ የፍልሰት ተመላሽ የሆነ ከወላጅ/ቤተሰብ የተነጠለ እና ወላጅ ያጣ ህፃን አማራጭ ድጋፍ እና እንክብካቤ አገልግሎት፤ እና

ረ/ የሥራ ቅጥር አገልግሎት ድጋፍ::

25. <u>እርከን ሦስት</u>

1) በዚህ እርከን ሥር የሚሰጥ የድጋፍ አገልግሎት ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች በቀጣይ ሊሰማሩበት የሚፈልጉት የሥራ መስክ መሠረት ያደረገ ሆኖ ወደ መደበኛ መኖሪያ አካባቢያቸዉ ከተመለሱበት ሶሰት ወራት ጊዜ ጀምሮ የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ/ ሊሠማሩበት በፈለጉት የሥራ መስክ የሚያስፈለግ በቂ የሙያ ክህሎት ስልጠና፤

ለ/ የማደራጀት እና ህጋዊ ሰውነት የማሰጠት ድጋፍ፤

ሐ/ ለመሥሪያ የሚሆን ቦታ ለሚያስፈልጋቸው የመሥሪያ ቦታ እንዲያገኙ መደገፍ፤

መ/ ለሥራ መነሻ የሚሆን ገንዘብ ለሚያስፈልጋቸው ከመደበኛ ብድር/ ተዘዋዋሪ ገንዘብ አቅርቦት፤

ሠ/ የመሳሪያ ሊዝ አቅርቦት፤

ረ/ የገበያ ትስስር አገልግሎት፤

ሰ/ የኢዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት፤ እና

ሸ/ የኢንተርፕራይዞች የሽግግር ድጋፍ ማዕቀፍ አገልግሎት።

## 26. <u>እርከን አራት</u>

1) በዚህ እርከን ሥር የሚሰጥ የድጋፍ አገልግሎት ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች በዘላቂነት እና በተረጋጋ መልኩ ህይወታቸዉን እንዲመሩ ለማስቻል የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ/ በተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ የማብቃት ድጋፍ አገልግሎት፤

ለ/ የክትትልና ድጋፍ አገልግሎት፤እና

ሐ/ ከድጋፍ ማዕቀፉ አብቅቶ ማሰናበት።

## 27. <u>የድጋፍ ሽግግር</u>

1) በሁሉም እርከኖች ላይ የክትትልና ድጋፍ ስራ ይከናወናል።

2) ከአንድ እስከ ሦስት ባሉ እርከኖች የሚሰጡ ድጋፎች በእርከኑ የትግበራ ጊዜ ውስጥ ካልተጀመሩ፣ ካልተጠናቀቁ እና የድጋፍ መቀጠል አስፈላጊ መሆኑ ድጋፍ በሚያደረገው አካል ሲታመንበት ድጋፉ በቀጣዩ እርከን የሚፈፀም ይሆናል።

## 28. <u>ድጋፉ ስለሚቆይበት ጊዜ</u>

ከላይ በእርክን ሦስት እና አራት ውስጥ የተዘረዘሩት ድጋፎች የአፈፃፀም ቆይታ ጊዜ በመደበኛው የሥራ እድል ፈጠራ ተቋማት አሠራር ሥርዓት የሚመራ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የተጎጂ ፍልሰት ተመላሾች መረጃ ቋት</u>

## 29. <u>መረጃ ቋት ስለማደራጀት</u>

1) የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ከውጭ ሀገራት በተለያየ ጊዜ ወደ ሀገራቸው የሚመለሱ ተጎጂ ከፍልሰት

ተመላሽ ዜጎች ዝርዝር መረጃ የሚያዝበት ሀገር አቀፍ ከፍልሰት ተመላሾች መልሶ ማቋቋም የመረጃ ቋት ያደራጃል፤ ያስተዳድራል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚደራጀው መረጃ ቋት በፌዴራል፣ በክልል፣ በዞን እና በወረዳ /ከተማ አስተዳደር ደረጃ ባሉ ባለድርሻ ተቋማት መካከል ትስስር የሚፈጥር መሆን ይኖርበታል።
3) ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች የመረጃ ቋት የተለያዩ ተቋማት በበይነ መረብ መረጃ ልውውጥ እንዲያደርጉ እና በተናጠል መረጃ ማስገባትና መተንተን እንዲችሉ ተደርጎ በኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት ጭምር ይደራጃል።
4) ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች የመረጃ ቋት ከብሄራዊ የፍልሰት መረጃ ቋት ስርዓት ጋር ተናቦና ተመጋግቦ እንዲሰራ ይደረጋል።

30. <u>ከፍልሰት ተመላሾች መረጃ ቋት ይዘት</u>

ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች የመረጃ ቋት ውስጥ የሚመዘገበው መረጃ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃ መያዝ አለበት፡-

1) ሙሉ ስም፣

   ሀ/ በፓስፖርት ወይም በይለፍ ወረቀት ላይ የተጻፈ ሥም እና

   ለ/ ወደ ውጭ ሀገር ከመሄዳቸው በፊት የሚጠሩበት ስም

2) ፆታ፣

3) የትውልድ ዘመን፣

4) የትምህርት ደረጃ

5) የትውልድ ቦታ፣

6) የጋብቻ ሁኔታ፣

7) ከሀገር የወጣበት ቀን፣ ወር እና ዓ.ም፣

8) ከሀገር የወጣበት ምክንያት፣

9) የነበረበት አገርና ከተማ፣

10) ከአገር የወጣበት ሁኔታ፣ በህጋዊ መንገድ ከሆነ የላከው ኤጀንሲ ሥምና አድራሻ ወይም በህገ-ወጥ ከሆነ የወጣበትን የመውጫ መስመር/በር፣

11) ወደ አገሩ የተመለሰበት ቀን፣ ወርና ዓመተ-ምህረት፣

12) ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ የሄደበት ክልል፣ ዞንና ወረዳ፣ ከተማና ቀበሌ፣

13) የተመላሹ ፎቶግራፍ፣

14) ከተመላሽ ጋር አብሮ የተመለሱ ልጆች (የተፈጥሮና የጉዲፈቻ ልጅ)፣

15) የደረሰበት የጉዳት አይነት እና ደረጃ፣

16) መረጃው በተወሰደበት ወቅት ተጎጂው የሚገኝበት ሁኔታ፣

17) የተጎጂ ከፍልሰት ተመላሽ ፍላጎት፣

18) የተጎጂ ከፍልሰት ተመላሽ ልምድና ክህሎት፤

19) ተመላሹ ድጋፍ ያገኘ ወይም ያላገኘ ስለመሆኑ፣

20) ድጋፍ ካገኘ ድጋፉን ያደረገለት አካልና የተደረገለት የድጋፍ አይነት እና

21) ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን።

31. <u>ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች መረጃ አሰባሰብ</u>

1) የተጎጂ ፍልሰት ተመላሽ ግላዊ መረጃዎችን በተመለከተ መረጃ አሰባሰብ ሂደቱ በተመላሹ ነጻ ፈቃድና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

2) የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በየጊዜው ከውጭ አገራት ወደ አገራቸው የሚመለሱ ዜጎች መረጃ ከኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቀብሎ ለሌሎች ተቋማት ያጋራል።

3) የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የተመዘገቡ የፍልሰት ተመላሾችን መረጃ አሰባስቦና አደራጅቶ ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ለሌሎች አግባብነት ላላቸው ተቋማት ያጋራል።

4) የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች ምዝገባና ያገኘውን የድጋፍ አይነት እንዲሁም ድጋፍ ስላደረገው ተቋም የሚሰበሰበውን መረጃ አስመልክቶ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፆችን ያዘጋጃል፤ የተዘጋጁትን ቅፆች አግባብነት ላላቸው የተለያዩ ተቋማት በመላክ መረጃውን በየጊዜው ይሰበስባሉ፤ ወደ መረጃ ቋት ያስገባል።

5) የመረጃ አመንጪ እና ተጠቃሚ ተቋማት የመረጃ ልውውጥ ፕሮቶኮል ወይም የመግባቢያ ሥምምነት በማዘጋጀት ይተገብራሉ።

32. <u>ተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች መረጃ ቋት አጠቃቀም</u>

1) የተጎጂ ፍልሰት ተመላሾች የመረጃ ቋት አጠቃቀም በተቻለ መጠን የተጎጂ ከፍልሰት ተመላሽ የግለሰባዊ መብት በማይነካና ምስጢራዊነቱ በተጠበቀ መንገድ መሆን አለበት፣

2) በየደረጃው የሚገኙ ለተጎጂ ፍልሰት ተመላሾች ድጋፍ የሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት በመረጃ ቋት መረጃ በቀላሉ ማግኘትና መጠቀም እንዲችሉ ይደረጋል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለድጋፍ ሰጪ ተቋማት አደረጃጀት</u>

33. <u>ስለድጋፍ ሰጪ ተቋማት አደረጃጀት</u>

1) በብሔራዊ የትብብር ጥምረት ስር የተደራጀው የተጎጂዎች እንክብካቤና መልሶ ማቋቋም የስራ ቡድን እና በየደረጃው የተደራጁት ተመሳሳይ አደረጃጀቶች በዚህ መመሪያ መሰረት የተጎጂ ከፍልሰት ተመላሾች ድጋፍ ስራዎችን ያስተባብራሉ፤ ይተገብራሉ።

2) የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እና በየደረጃው የሚገኙት የሥራ ዕድል ፈጠራ የሚያስተባብሩ ተቋማት የስራ ቡድኑ ሰብሳቢ በመሆን ያስተባብራሉ።

3) የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በየደረጃው የሚገኙ ተመሳሳይ ተቋማት ጸሐፊ ይሆናሉ።

34. <u>የክትትልና ግምገማ ሥርዓት</u>

በየደረጃው ያለው የተጎጂዎች እንክብካቤና መልሶ ማቋቋም የሥራ ቡድን የሚከተሉትን የክትትልና ግምገማ ተግባራት ያከናውናል፡-

1) ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ በአባል ተቋማት አስገምግሞ ካጸደቀ በኋላ ለፈጻሚ ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ያደርጋል፤
2) በየደረጃው ካሉ አካላት በየሩብ አመቱ ሪፖርቶች እንዲቀርቡ ያደርጋል፤
3) በየ6 ወሩ የመስክ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
4) በዓመት ሁለት ጊዜ የግምገማ መድረክ ያዘጋጃል፤
5) የተጎጂዎች እንክብካቤና መልሶ ማቋቋም ስራዎች ናሙና በመውሰድ የዳሰሳ ጥናት ያደርጋል፤
6) ይህ መመሪያ በትክክል ስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤ የተገኙ ውጤቶችና ያጋጠሙ ችግሮችን ይለያል፤ የመፍትሔ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
7) ምርጥ ተሞክሮችን በመቀመር እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
8) በዚህ አንቀጽ መሠረት ያከናወናቸውን ተግባራት በየደረጃው ለሚገኙ የትብብር ጥምረቶች ሪፖርት ያቀርባል።

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

35. <u>የሌሎች ህጎችና አሰራሮች ተፈጻሚነት</u>

ከተመላሾች ጋር በተያያዘ የወጡ መመሪያዎችና የአሰራር ስርዓቶች ከዚህ መመሪያ ጋር ተጣጥመው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

36. <u>ስለተሻሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

**ተጎጂ ከስደት ተመላሽ ዜጎችን መደገፊያና መልሶ ማቋቋሚያ መመሪያ ቁጥር** 65/2011 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

37. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም አካል ይህን መመሪያ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት።

38. <u>የህግ ተጠያቂነት</u>

በዚህ መመሪያ ሀላፊነት የተሰጣቸው አካላት ሃላፊነታቸውን ካልተወጡ አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናሉ።

39. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከግንቦት 23 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

**አዲስ አበባ**

**ግንቦት 23 ቀን 2015 ዓ.ም**

**ጌድዮን ጢሞቲዮስ (ዶ/ር)**

**የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስትርና**

**የብሄራዊ ትብብር ጥምረት ሰብሳቢ**